# የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ(አንድነት)
# ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ የአቋም መግለጫ

ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በተካሄደው መስራች ጉባኤ የመሰረትነው አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲያችን ከሊቀመንበራችን እስር በኋላ ህልውናው አደጋ ላይ መውደቁ ያሳሰባቸው በፓርቲው የተለያዩ መዋቅሮች ውስጥ የሚገኙ አባላት 1/3ኛ የጉባኤ አባላትን ፊርማ በማሰባሰብ የጠሩት ልዩ ጠቅላላ ጉባኤ የቀረበለትን ሪፓርት አዳምጦ፣ በአጀንዳዎች ላይ ከተወያየና ውሳኔ ካሳለፈ በኋላ ይህን የአቋም መግለጫ አውጥቷል፡፡

1. የአንድነትን ህልውና ለመታደግ የተካሔዱት ጥረቶች ሁሉ ፍሬ አልባ የሆኑት አመራሩ ለውይይት እምቢተኛ በመሆኑ እንደሆነ ጉባኤው ተገንዝቧል፡፡ የፓርቲው የመጨረሻ ውሳኔ ሰጪ የሆነው ይህ ጉባኤ የፓርቲውን ህልውና እንዲታደግ መጠራቱም ተገቢና ትክክለኛ ርምጃ፣ አጠራሩም ህጋዊ መሆኑን ይህ ጉባኤ አረጋግጧል፡፡ ተነሳሽነቱን ወስደው አንድነትን ለማዳን ጥረት ያደረጉትን፣ ይህን ጉባኤ የጠሩትንና ያሳኩትን አባላትም ጉባኤው ከልብ አመስግኗል፡፡
2. ብ/ም/ቤቱ በመተዳደሪያ ደንቡ የተጣለበትን ኃላፊነት ያለመወጣቱን፣ የመስራች ጉባኤውንም ውሳኔዎች ተፈፃሚ ያለማድረጉን፣ በዚህ አድራጎቱም ሥራ አስፈፃሚውና አንዳንድ የአመራር አባላት ከህግና ስርዓት ውጭ እንዲሰሩ ያደረገ መሆኑን ይህ ጉባኤ ተገንዝቦ ምክር ቤቱን በአዲስ መልክ አዋቅሯል፡፡
3. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ለፓርቲው ህግ ተገዥ ባለመሆኑና የአሰራር መርሆዎችን በመጣስ የፈፀመውን፣ አባላቱን አባርሬያለሁ ማለቱን፣ ህገወጥ ቅጥርና ማባረር መፈፀሙን፣ ገንዘብ አላግባብ መጠቀሙን፣ የፓርቲ ፕሮግራም መለወጡንና በምርጫ በሚያዙ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሰዎችን መሾሙን ጉባኤው በጥብቅ እያወገዘ ይህን የፈጸመውን አመራር ለውጧል፡፡
4. የፓርቲያችን ፕሮግራም እየተሻሻለ መሄድ የሚገባው መሆኑ ቢታመንም አመራሩ አንድን ግለሰብ አባል ለማድረግ ሲል ብቻ የፓርቲውን ደንብ ባላከበረ ሁኔታ ፕሮግራሙን መለወጡን ጉባኤው አጥብቆ እያወገዘ የአንድነት ፕሮግራም ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በመስራች ገባኤው የፀደቀው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ከዚህ በኋላም ያለ ጠቅላላ ጉባኤው ይሁንታ የፓርቲው ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በማናቸውም የስልጣን አካላት እንዳይለወጥ ጥብቅ ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡
5. አንድነት መድረክ ውስጥ የገባበት ሁኔታ በሪፖርት ከቀረበው በተጨማሪ በየአካባቢው ተፈጥረው ከተመለከታናቸው ችግሮች አንፃር ተገቢና ትክክለኛ አለመሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም አዲሱ ምክር ቤት ጉዳዩን እንደገና መርምሮ የአንድነትን መሰረታዊና ህብረ ብሔራዊ አላማዎች ባስከበረ መልኩ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ኃላፊነት ተሰጥቷል፡፡
6. የሊቀመንበራችን ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ይቅርታ የተነሳውና ለእስር የተዳረገችበት ሁኔታ ህገወጥ መሆኑን ጉባኤው ተገንዝቧል፡፡ በመሆኑም ለሐገራችን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የሚበጀው የአንድ ሀገር ልጆች እጅ ለእጅ ተያይዘን ስንሰራ እንጅ አጥፊና ጠፊ ሆኖ በመሰለፍ ስልጣንን

ለበቀልና ራስን ብቻ ለሀገር አሳቢ አድርጎ በማቅረብ ያለመሆኑን በመገንዘብ መንግስት ሊቀመንበራችንን በአስቸኳይ እንዲፈታ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡

7. የአንድነት አመራር ሊቀመንበራችን በፖሊስ በተጠራችበት ወቅት የራስሽ ጉዳይ ማለቱና ከጎኗ ሊቆም አለመቻሉ ፤ የብርቱካንን እስር ለምርጫ ቅድመ ሁኔታ አድርገን እናቀርብም ካለ በኋላ ፎቶግራፏን በመያዝ "ብርቱካን እንድትፈታ መድረክን ምረጡ" እያሉ በስሟ መነገድ ጉባኤተኛውን በእጅጉ አሳዝኗናል በግል የድርጊቱ ዋና ተዋናይ የሆኑት አመራሮች ይህንን አሳፋሪ ተግባር ሲፈፅሙ ለማስቆም ጥረት ያላደረገዉን ብሔራዊ ምክር ቤት ጉባኤው ተጠያቂ አድርጎታል::
8. አንድነት ከመነሻው ይዞት የተነሳው ዓላማ ሳይበረዝና ሳይከለስ ተግባራዊ እንዲሆን በጥብቅ እያሳሰብን ተመራጩ ምክር ቤት ይህን ሃላፊነት በብቃት እንዲወጣ አደራ እንላለን::
9. በዛሬው ዕለት የፓርቲው ከፍተኛ የስልጣን አካል የሆነው ይህ ጠቅላላ ጉባኤ አመራሩን የቀየረ በመሆኑ እስከ አሁኑ ሰዓት በአንድነት አመራር ስም የተቀመጡ ግለሰቦች የፓርቲውን ገንዘብና ንብረት በኦዲት አስመርምረው ለተመረጠው አዲስ አመራር እንዲያስረክቡ ጉባኤው ወስኗል::
10. በመጨረሻም ለቃሏ ታማኝ፤ ለዕምነቷ ፅኑ የሆነችውና በተግባር ያስመሰከረችው ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ትናንትም፣ ዛሬም ሆነ ነገ የአንድነት ሊቀመንበር መሆኗን እናረጋግጣለን::

ሚያዚያ 10 ቀን 2002 ዓ.ም<br>
ኮከበ ፅባህ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት<br>
አዲስ አበባ